ግዜ
ግንቦት 7 ዜና
የግንቦት 7 ድምጽ
www.ginbot7.org

እሮብ ግንቦት 20 2000 ዓ.ም

## በአምባገነኑ በኮነኔል መንግስቱ /ማርያምና የተላለፈው የሞት ቅጣት አነጋጋሪ ሆኗል፡፡

ሰኞ ግንቦት 18 2000 ዓ.ም ያስቻለው የመለስ ዜናዊ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በቀድሞው ርእሰ-ብሄር በአምባገነኑ በኮነኔል መንግስቱ /ማርያምና በቅርብ ባልደረቦቹ ላይ የሞት ቅጣት በይኗል፡፡ ‹‹ይህ ውሳኔ ለረጅም ግዜ ሲጓተት ቆይቶ ባሁኑ ወቅት የተሰጠበት የራሱ ምክንያት አለው›› የሚሉ በርካታ ናቸው፡፡ ወያኔ ኢህአዴግ ሁሌም እንደሚያደርገው በሀገር ውስጥ ውጥረትና ቀውስ ሲገጥመው፣ የህዝብንና የአለም-አቀፉን ህብረተሰብ የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር ድንገተኛ የሆነ ዜና ያፈነዳል፡፡ ድርጊት ይፈጽማል፡፡ ህገ ወጡ የሶማሌ ወረራ ከሌሎች ምክንያቶች በተጨማሪ በሃገር ውስጥ የሚያኪያሄደውን የጅምላ እስራትና ግድያ ለመሸፍን የተደረገ እንደነበር የሚያስታውሱ ብዙ ናቸው፡፡ የቅርቡ የከተማ የቦንብ ፍንዳታና አሁን ደግሞ በቀድሞው ፕሬዚደንትና በባልደረቦቹ ላይ ፍርድ ቤቱ ያስተላለፈው የሞት ቅጣት ውሳኔ፣ የመለስ ዜናዊና የበረከት የማፍያ አገዛዝ በስሌት የፈጸማቸው ድርጊቶች ናቸው እየተባለ ነው፡፡ ህዝብ በኑሮ ውድነትና በድርቅ በሚሰቃይበት፣ በሱዳን በኩል የሃገሪቱ ምድር ለባእዳን ተቆርሶ በመሰጠቱ ህዝብ በሚጮህበት፣ በሱማሌ በኩል የስልጣን እድሜ ለማራዘሚያ የሚሆን የአሜሪካኖችን የገንዘብና የቁሳቀቁስ ድጋፍ ለማግኘት እንደዋዛ የተገባበት ጦርነት ማጠፊያው ባጠረበት በአሁኑ ወቅት፣ የህዝቦን የትኩረት አቅጣጫ ለማሳት ይህንን የፍርድ ቤት ውሳኔ ካድሬ ዳኞች በትእዛዝ እንዲፈጽሙ መደረጋቸው ታውቋል፡፡ የወያኔ ስሌት የአለም አቀፍን ህብረተሰብ በጥቂቱም ለማወናበድ የቻለ ለመሆኑ የተለያዩ አለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሃን ለዜናው በተሰጡት ሽፋን የታየ ሆኗል፡፡ ሃገሬውን በሚመለከት ግን የወያኔ ሴራ የተፈለገውን ኢላማ አልመታም፡፡ ነገሩ ‹አመድ በዱቄት ይስቃል› ሆኗል ይላል ህዝቡ፡፡ ህዝብ ‹አንዱ ነፍሰ ገዳይ በሌላው ነፍሰ ገዳይ ላይ ብይን የመስጠት የሞራል ብቃት የለውም› እያለ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ፍትህ አለ ብሎ የሚያምነው በወደቀ አምባገነን ላይ ብይን መስጠት ሲቻል ሳይሆን ባለስልጣናቱ በስልጣን ላይ እያሉ በሃገርና በወገን ላይ ወንጀል ሲፈጽሙ ለፍርድ ማቅረብ የሚቻልበት ሁኔታ ሲኖር ብቻ እንደሆነ ተችቶበታል፡፡ ይህ ለማዘናጊያ የተወረወረ የወሬ ሙዳ፣ መለስ በሃገራችን ላይ ያከሄደውን ክህደት፣ በሃገር ላይ የነገሰን ረሃብና የኑሮ ውድነት፣ በጥቂቶች የሚካሄደውን ዘረፋ ለአንድ ደቂቃም ቢሆን እንዲረሳው የማያደርገው መሆኑን የተለያዩ ዜጎችን በማነጋገር የተላከልን ዘገባ ያመለክታል፡፡